# *“. . . ዘመኑን ዋጁ! ”*

*ሰዎች የጠፋባቸውን ዕቃ ለማግኘት የዕቃውን ዓይነት፣ የጣሉበትን ሥፍራና ላገኙላቸው ሰው የሚሰጡትን ወሮታ ገልፀው ማስታወቂያ በሚለጥፉበት የአፋልጉኝ ሰሌዳ ላይ እንዲህ የሚል ጽሁፍ ይነበባል፡፡*

> *“ትናንት፤ በፀሐይ መውጣትና መጥለቅ መካከል ወርቅ የሆኑና እያንዳንዳቸው በስልሳ፤ ደቂቃዎች ያሸበረቁ ሁለት ሰዓታት ጠፍተውብኛል፡፡ ላገኘልኝ ሰው የምከፍለው ምንም ወሮታ የለም፤ ዳግም ላይገኙ ለዘላለም ጠፍተዋልና፡፡”*

*የሚል፡፡ ይህ ማስታወቂያ አንድ ሰው  ከአንድ ቀን በፊት ስላባከናቸው ሁለት ሰዓታት የጻፈው ፀፀት አዘል አቤቱታ ነው፡፡*[1]
*አበው እንደሚሉት ‹‹ጊዜ ወርቅ›› ነው፡፡ ነገር ግን እንደ ወርቅ አይገዛም፣ አይሸጥም ወይም አይለወጥም፤ በባንክ አይቀመጥም ወይም ለሌላ ሰው በብድር አይሰጥም፡፡ ጊዜ በጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ ካልዋለ በስተቀር ይባክናል፤ ለዘላለምም ይጠፋል፡፡ በዚህ ምድር ላይ ለሁሉ እኩል የተሰጠ ነገር ቢኖር ጊዜ ብቻ ነው፡፡ የማይክሮ ሶፍት ባለቤት ቢል ጌት እና አንድ የጎዳና ተዳዳሪ እኩል ሃያ አራት ሰዓታት፤ እኩል ሰባት ቀናት እንዳላቸው ማሰብ አያስገርምም? ሁለቱ በጊዜ አጠቃቀም እንጂ በጊዜ መጠን አንዱ ከሌላው በሰኮንድ እንኳ ፈፅሞ አይበላለጡም፡፡ ጊዜ ዕድል ነው፡፡ ታዲያ ቁም ነገሩ ባለ ዕድል መሆን ብቻ ሳይሆን ዕድልን በአግባቡ በመጠቀም ሊደረስ የሚገባው ሥፍራ መድረስ ነው፡፡ ጊዜ ሕይወት ነው! በሕይወት እስካለን ድረስ ጊዜ አለን፤ በምድር ላይ ጊዜ የማይኖረን ከምድር ስንለይ ብቻ ነው፡፡ ጊዜ ልንጠቀምበት የምንችል ሃብት ብቻ ሳይሆን፤ የምንጠየቅበትም ኃላፊነት ነው፡፡ ታዲያ በዐይናችን ፊት በቅፅበት እየከነፈ ስላለው ጊዜያችን ምን እያሰብን ይሆን?*
*በጅማሪዬ ላይ ስለ ጊዜ ይህን ያልኩት ያለምክንያት አይደለም፡፡ የፈረንጆቹ* 2008 *ለ* 2009 *ስፍራ ሊለቅ ጥቂት ቀናት በቀሩበት በዚህ ወቅት ስለጊዜ አጠቃቀም ብርሃን ሊፈነጥቅልን የሚችል ሃሳብ ከኤፌሶን* 5፡-15-21 *ላካፍላችሁ ከጅዬ ነው፡፡*

## *<u>መመላለስ</u>*

> *‹‹እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ›› ኤፌ.*4፡1

*ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ከምዕራፍ አንድ እስከ ሶስት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ስላበሠረው ታላቅ ጥሪ በጥልቀት ከዘረዘረ በኃላ ከምዕራፍ አራት  ቁጥር አንድ በመነሳት እስከ መልዕክቱ መደምደሚያ ድረስ ለዚህ ታላቅ ጥሪ እንደሚገባ ስለመመላለስ  ይጽፋል፡፡ በዚህ ተግባራዊ ኑሮ ላይ ባነጣጠረ ሁለተኛ ክፍል ውስጥ  መሪ አድርጎ የተጠቀመበት ቃል ‹‹መመላለስ›› የሚል  ነው፡፡ ይህን ቃል ቀደም ባለውና መሠረታዊውን የክርስትና ትምህርት ባሰፈረበት የመጀመሪያ ክፍል ሁለት ጊዜ ተጠቅሞበታል፡፡* 2፡2 *ላይ የሰፈረው፤ የቀድሞውን አሮጌ ኑሯችንን ለማመልከት ሲሆን በኤፌ* 2፡10 *ላይ የሚገኘው ደግሞ አዲሱንና በክርስቶስ ያለንን ሕይወት ለማመልከት*

[1] Stott, John R. W: The message of Ephesians, P. 202

የተጠቀመበት ነው፡፡ *ታዲያ* ሁለቱም ስለ ‹‹*መመሳለስ*›› የሚናገሩ ናቸው፡፡ ሐዋርያው ይህንን *መሠረት* በማድረግ በሁለተኛው ተግባራዊ ክፍል ውስጥ ይህንን *ቃል* አምስት ጊዜ በመጠቀም *መልዕክቱን* ወደ አንባቢያኑ ልብ ለማድረስ ጽፏል፡፡ በ 4፡1 ላይ *‹‹. . . በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ፡፡››* በ 4፡17 ላይ *‹‹ . . . እንግዲህ አህዛብ ደግሞ በአዕምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱ ከእንግዲህ ወዲህ እንዳትመላለሱ እላለሁ በጌታም ሆኜ እመሰክራለሁ፡፡››* በ 5፡2 ላይ *‹‹. . . ክርስቶስም ደግሞ እንደወደዳችሁ ለእግዚብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባዕንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ፡፡››* በ 5፡10 *‹‹ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ . . .››* በመጨረሻም በ 5፡15 ላይ *‹‹ እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ፡፡››* በማለት በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ የእግዚአብሔርን ሕይወት የተካፈሉ ቅዱሳን በዚህ ምድር ላይ እንዴት ሊመላለሱ እንደሚገባ መለኮታዊ ምክር ይፅፋል፡፡ የሚፅፈውም በክርስቶስ የአዲሱ ሰው ዘር ለሆኑት በኤፌሶን ለሚገኙት ቅዱሳን ነው፡፡ አዲስ ሰው አዲስ የኑሮ *ሥርዓት* ያስፈልገዋልና፤ በክርስቶስ በማመን አዲስ ፍጥረት የሆኑ ሁሉ አሮጌውን የኑሮ *ሥልት* አውልቀው ጥለው አዲሱን እንዲጎናፀፉ ይመክራል፡፡

የሐዋርያውን ሃሳብ በብቃት ለመረዳት በቅድሚያ «*መመላለስ*» የሚለውን *መሪ ቃል* እንመልከት ‹‹*መመላለስ*›› ለእርምጃችን ሞተር የሆነውን የተለወጠ አስተሳሰብን፣ አካሄድን፣ የኑሮ ዘይቤን ባጠቃላይ በምድር ላይ ያለንን ሕይወት የሚገልፅ *ቃል* ሲሆን በሰማያት በአባቱ ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ በምድር በእኛ ውስጥ ሊኖር የሚፈልገውን ሰማያዊ የኑሮ ዘዬ የሚያመለክት ነው፡፡

ስለመመላለስ ከተዘረዘሩት አምስት ነጥቦች መሃከል በዚህ ጽሁፍ ላተኩርበት የፈለኩት አምስተኛውና ስለ ጊዜ አጠቃቀም የሚናገረው ክፍል ነው፡፡ በዚህ ክፍል ሐዋርያው ለጥሪያችን በሚመጥን መልኩ በጥበብ መመላለስ እንደሚገባን፤ ይህም ጥበብ የቀኑን ክፉት አውቀን ዘመኑን መዋጀት እንደሆነ፤ ዘመኑን ለመዋጀት የጌታን ፈቃድ ማስተዋል እንደሚጠይቅና የጌታም ፈቃድ አንዳች ጊዜ ሳናባክን እርስ በርሳችን በመተናነፅና እግዚአብሔርን በማመስገን እየኖርን በሚያልፍ ጊዜ የማያልፍ ተግባር ማከናወን እንደሆነ ይጽፍልናል፡፡

## <u>ጥበብ</u>

> *‹‹እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ ተጠበቁ፡፡›› 5፡15*

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል ጥበብን የገለጸው ከጊዜ ጋር በማያያዝ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ዐይን ጥበበኛ የሚባለው ሰው ጊዜውን በአግባቡ በመጠቀም የሚመላለስ ሰው እንደሆነ ይነግረናል፡፡ እግዚአብሔር በጊዜ ውስጥ አይኖርም ነገር ግን ጊዜን ፈጥሮአል፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ከሰጠው ትልቅ *ሥጦታ* መሃል ጊዜ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ የእግዚአብሔር ድርሻ ጊዜን መስጠት እንጂ መጠቀም አይደለም፡፡ ጊዜን በጥበብ መጠቀም የሰው ድርሻ ነው፡፡ ጊዜን በጥበብ መጠቀም ስንል በአንዴ ብዙ *ሥራ* መስራትና ያለ ዕረፍት መባዘን ሳይሆን፤ በሚያልፍ ጊዜ የማያልፍ *ሥራ* በመሥራት ጊዜ ዘላለማዊ ፋይዳ እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡

በዚህ ክፍል ጥበበኞች እንድንሆን እየተመከርን ነው። ጥበበኞች ነን? ጥበበኞችስ መሆን እንችላለን? ጥበበኛ ሐዋርያው በሌላ ስፍራ ስለ መጠራታችን ሲናገር እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች እንዳልተጠሩ ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር እንደመረጠ፤ በግልፅ ነግሮናል።[2] ታዲያ በዓለም ጥበበኞች ዓይን እንደ ሞኝ መታየታችን ለመመረጣችን ምክንያት ከሆነና እኛም ሞኝነታችንን በፀጋ ከተቀበልን ጥበበኞች መሆን ለምን አስፈለገን? መልሱን እነሆ፤ እግዚአብሔር የዓለምን ሞኞች የመረጠው የሞኞች ማሕበር ለማቋቋም ፈልጎ ሳይሆን በዓለም ሚዛን ሞኞች በተባልነው ውስጥ ጥበቡ የሆነውን ክርስቶስን በመግለጥ የዓለምን ጥበበኞች ለማሳፈር ፈልጎ ነው። ስለዚህ ስንጠራ ሞኞች የነበርን ብንሆንም ሞኝ ሆነን መቅረት አይኖርብንም። በሞኝነት ጥበብን ማሳፈር የማይቻል ነውና። ይልቅ በእርሱ እንድንመካ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብ ሆኖ የተሰጠንን ክርስቶስን በኑሯችን ሁሉ በመግለጥ ከዓለም እጅግ በላቀ ሰማያዊና መለኮታዊ ጥበብ መመላለስ ይጠበቅብናል። ይህም ጥበብ የሚሻሩት የዚህ ዓለም ገዥዎች ጥበብ ሳይሆን እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን የወሰነውና ተሰውሮ የነበረው አሁን ግን የተገለጠው የእግዚአብሔርን ጥበብ ነው።[3] ይህ ጥበብ የሚገለጥባቸው በርካታ መንገዶች ቢኖሩትም ጊዜን በአግባቡ መጠቀም አንዱና ዋነኛው ነው። ጥበብ የዕድሜ ዘመንን ከማወቅ፤ ከመለካትና በአግባቡ ተምኖ ከመጠቀም ጋር ጽኑ ተዛምዶ እንዳለው በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ የሰፈረውና የእስራኤልን ልጆች የምድረበዳ ጉዞ አስመልክቶ የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ የጻፈው የጸሎት መዝሙር ድንቅ ብርሃን ይፈነጥቅልናል።

*‹‹የዕድሜያችን ዘመን ሰባ ዓመት ቢበዛም ሰማንያ ነው፤ ከዚያም በላይ ከሆነም ድካምና መከራ ብቻ ነው፤ ቶሎ ያልፉልና፤ እኛም ወዲያው እንነጉዳለን። . . . ጥበብን የተሞላ ልብ ይኖረን ዘንድ ዕድሜአችንን መቁጠር አስተምረን።›› መዝ.90፡12 (አ.መ.ት)*

በምድር ላይ የምንኖርበት ዘመን ውስን እንደሆነ፤ ነገር ግን በዚህ ውስን ዘመን ጊዜያዊ ስሜታችንን ለማርካት ከመጣደፍ ይልቅ ለዘላለም የሚበጀንን መስራት እንዳለብን የሚያስገነዝበው ጥበብ ከሰው ልጆች እንደሰማይ መራቁን ለመረዳት በዙሪያችን ያለውን የሰው ልጆች እንቅስቃሴ በእዝነ- ልቦናችን ለአፍታ ማጤን ይበቃል። እያንዳንዱ ሰው የሚመላለሰው በምድር ላይ የዘላለም ዕድሜ እንዳለው እያሰበ ነውና። ምናልባት ጠቢቡ ንጉስ ሰለሞን *‹‹ወደ ግብዣ ቤት ከመሄድ ወደ ሃዘን ቤት መሄድ ይሻላል፤ ሞት የሰው ሁሉ ፍፃሜ ነውና፤ ሕያው የሆነም ይህንን ልብ ማለት ይገባዋል፤ . . . የጠቢባን ልብ በሃዘን ቤት ነው፤ የሞኞች ልብ ግን በደስታ ቤት ነው።›› መክ.7፡2፣4 (አ.መ.ት)* ያለው ዘመንን በማወቅና በጥበብ መሃከል ያለውን ጥብቅ ቁርኝት ለመዘከር ይሆን?

በዚህ ምድር ስንኖር ሁለት ነገሮች ተሰጥተውናል፤ አንድ አከናውነን ልንፈፅመው የሚገባን *ሥራ*፤ ሁለት ይህን *ሥራ* ልናከናውን የምንችልበት ዘመን ወይም ዕድሜ። ሲጀመር *ሥራ*ውና ዕድሜው እኩል ናቸው፤ አፈፃፀማቸው ግን በአብዛኛው እኩል አይሆንም፤ ዕድሜ ሲያልቅ ሊከናወን የሚገባው *ሥራ* ገና አይጋመስም። እግዚአብሔር የነዌን ልጅ እያሱን *‹‹አንተ ሸመገልህ በዕድሜህም አረጀህ ያልተወረሰች እጅግ ብዙ ምድር ገና ቀርታለች . . .›› ኢያሱ13፡1* እንዳለው ነው። በሩጫ ውድድር አንድን ተወዳዳሪ አሸናፊ የሚያደርገው እንዲሸፍን የተሰጠውን ርቀት በተሰጠው የጊዜ ገደብ መጨረሱ እንደሆነ ሁሉ፤ እኛንም በሚመጣው ዘመን የሚያሸልመን በተሰጠን ውስን የዕድሜ ዘመን፤

---

[2] 1ቆሮ. 1፡26-31
[3] 1ቆሮ. 2፡7

ልናከናውነው የተሰጠንን *ሥራ* በመፈፀማችን ነው፡፡ ለዚህ አይደል ቅዱስ ጳውሎስ የምድር ቆይታውን ሊያገባድድ በተቃረበበት ወቅት *ሥራውንም* እኩል እንደጨረሰ በድል ሲያውጅ *‹‹ሩጫውን ጨርሻለሁ . . . ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል . . .›› 2ጢሞ.4፡6-8* የሚለው፡፡ *ታዲያ* ይህ ጥበብ ከየት ይገኛል? ሳይነቅፍ በልግስና የሚሰጠውን እግዚአብሔርን በእምነት በመለመን እንደሆነ ያዕቆብ *‹‹ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን ለእርሱም ይሰጠዋል›› ያዕ.1፡5* በማለት ይነግረናል፡፡ ስለዚህ እኛም ከሙሴ *ጋር ‹‹ጥበብ የተሞላ ልብ ይኖረን ዘንድ ዕድሜያችንን መቁጠር አስተምረን››* ከማለት ውጭ ምን አማራጭ አለን?

## *ዘመንን መዋጀት*

*‹‹ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ›› ኤፌ.5፡16*

ቀኖች ሰባት ስም ወጥቶላቸው አንዱ ከሌላው ቢለዩም እንኳ በ*መካከላቸው* አንዳች ልዩነት እንደሌለ *መረዳት* አያስቸግርም፡፡ አንዱ ቀን ከሌላው ክፉም ደግም *መሆን* አይችልምና፡፡ ቀንን ክፉም ደግም ሊያደርገው የሚችለው ሰዎች በውስጡ የሚሰሩት *ሥራ* ብቻ ነው፡፡ ይህም አንድ ሰው ብቻውን የሚሰራው መልካምና ክፉ *ሥራ* ብቻ ሳይሆን ማሕበረ-ሰብ በጋርዮሽ የሚሰራው ከዚያም በቡድን አንዳንዴም በግለ-ሰብ የሚገለጥ ተግባር ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ፡ - *‹‹ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል›› ማቴ.6፡34* ሲል ነገ የተለየ ክፉ ቀን መሆኑን ለመግለፅ ሳይሆን ከላይ ሲናገር እንደነበረው *(ማቴ.6፡18-34)* ሰዎች የክፋት ሁሉ *ሥር* የሆነውን ገንዘብን በመውደድ፤ በምኞት ተነድተው ለነገ የቀጠሩት ቀኑን የሚያስጨንቅ አያሌ እኩይ ተግባር መኖሩን ለማመልከት ነው፡፡ ይህም ክፉ ሃሳብ የአመፅ መሣሪያ በሆኑ ሰዎች አዕምሮ ውስጥ በሃሳብ ተፀንሶ በድርጊት ከመወለዱ በፊት ዘሩ የሚመነጨው የጨለማው ዓለም ገዥዎች በሆኑ የክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ውስጥ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ ክፋት ከዲያቢሎስ ልብ መንጭቶ *ሥጋ*ና ደም በሆኑ ሰዎች ውስጥ በመገለጥ ቀኑን ክፉ ያደርገዋል፡፡ ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን መልዕክት 6፡12 እና 13 ላይ መጋደላችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከመንፈሳዊ የክፋት ኃይላት ጋር እንደ ሆነ ከገለፀ በኋላ *‹‹ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም ሁሉንም ፈፅማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሱ፡፡››* በማለት ስለ ቀኑ ክፋት የሚጽፈው፡፡ ክፋት ከሰው ልጅ ውድቀት ጀምሮ በምድር ላይ የነበረ ቢሆንም የመገለጡ መጠን ግን በምድር ላይ የሰው ቁጥር ከመብዛቱና አመለካከቱ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለዲያቢሎስ ከመመቸቱ እንዲሁም ፈሪሃ እግዚአብሔር ከትውልድ ከመራቁ ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ስልጣኔ በራሱ መልካም ቢሆንም እግዚአብሔር አልባ ስልጣኔ በምድር ላይ ሲንሰራፋ ክፋትም እየሰለጠና እየረቀቀ ከትናንት ዛሬ፤ ከዛሬ ነገ እየባሰ መሄዱ አሌ የማይባል ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ጳውሎስ እርሱ የኖረበትን አንደኛውን ክፍለ ዘመን ክፉ ካለው አሁን እኛ ያለንበት ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ምንኛ የከፋ ይሆን?

ሆኖም ይህ በየቀኑ የሚገለጥ ክፋት ያለ ፍፃሜ አይቀጥልም፡፡ ምንም እንኳ በየዕለቱ እየጨመረና እየባሰ ቢሄድም እግዚአብሔር በኪነ-ጥበቡ የፍፃሜ ቀን መድቦለታል፡፡ ያም ቀን ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ የሚገለጥበት የተባረከ ቀን ነው፡፡

እስከዚያም ድረስ ዓመፅ በነፃ አልተለቀቀም የሚከለክል አለና።[4] ከክፋት የተዋጀንና የአዲሱ ሰው ክፍል የሆንን እኛ ዘመኑን በመዋጀት ውስጥ ግዙፍ ድርሻ እንዳለን ልብ ልንል ይገባል። አዎን ቀኖች ፈፅሞ ክፉ እንዳይሆኑ ማድረግ አንችልም። ሆኖም ከፊታችን ያሉ ቀኖች ሙሉ በሙሉ በክፉው እጅ እንዳይወድቁና የክፋት መናኸሪያ እንዳይሆኑ ትልቅ ሚና ልንጫወት እንችላለን። ይህንንም ለማድረግ በተራ ቁጥር አንድ የሚቀመጠው ጉዳይ ከክፋት መራቅና ከማናቸውም ክፋት ጋር አለመተባበር ነው። የምንደግፈውን ልንቃወም የምንገነባውንም ልናፈርስ አንችልምና። ለዚህ ነው ጳውሎስ ቀደም ብሎ፦ *‹‹እንግዲህ ከእነርሱ ጋር ተካፋዮች አትሁኑ . . .›› ኤፌ.5፡7* ያለው። በማንኛውም ቀን ቴሌ-ቪዥን ስንከፍት፤ ሬዲዮ ስንጎረጉር ወይም ጋዜጣ ስናገላብጥ የክፋትን መዓት እስኪያንገሸግሸን እንጋታለን። ይህም ሊገለጥ የቻለው ብቻ ነው እንጂ ሁሉንማ ማን ሊተርከው ይችላል! ታዲያ ከጋዜጠኞቹ ድምፅ ባሻገር ያለውን የዘመኑን ድምፅ ማዳመጥ ለቻለ ቀኑ በጣር ይጮኻል፤ በሲቃም ይጣራል፤ የነፃ አውጪ ያለህ! ይላል። የሚጣራውም ወደ እግዚአብሔር ሳይሆን ወደ ሰው ነው። ያውም ወደ እግዚአብሔር ልጆች። ወደ ፊትስ ቢሆን ያለ ፈቃዱ ከተገዛበት የጥፋት ባርነት አርነት ወጥቶ ወደ እውነተኛ ነፃነት ለመድረስ ተስፋ የሚያደርገው የእግዚአብሔርን ልጆች ክብር መገለጥ አይደል![5] ያ ቀን ደርሶ በእኛ በሚገለጠው የእግዚአብሔር ክብር ነፃነት እስኪምበሸበሽ ድረስ ዛሬም ፀጋ በበዛልን መጠን ከክፉው እጅ እንድንናጠቀው በመቃተት ይጠብቃል። እንዴት? ዲያቢሎስ ጥቂት ጊዜ ብቻ እንዳለው ጠንቅቆ ያውቃል። ስለዚህ ጊዜ እንዳለቀበት አውቆ በታላቅ ቁጣ በምድር ላይ ይሠራል። ሃሳቡን በምድር ላይ የሚፈፅሙለት፤ በእርሱ ፈቃድ የሚመላለሱትም ሰዎች ፈፅሞ ፋታ የላቸውም። አውቀውትም ይሁን ሳያውቁት ያለመድከም ያቅዳሉ፣ ያለመታከት ያከናውናሉ። ሰይጣን በባሕሪው ችላ የሚለውና በከንቱ የሚያሳልፈው አንዳች አጋጣሚ የለም። ያገኘውን ዕድል ፈንታ ሁሉ ይጠቀማል። ታዲያ በምድር ላይ የክርስቶስ እጅና እግር የሆንን እኛ በዳተኝነት የምናንቀላፋው ስለምንድን ነው? በዐይናችን ፊት በርካታ ዕድሎችና አጋጣሚዎች እያለፉ የማንጠቀምባቸውስ እስከመቼ ነው? በዚህ ክፍል ላይ በግልፅ እንደተቀመጠልን ዘመኑን መዋጀት የእኛ ድርሻ ነው። ብዙዎቻችን የእግዚአብሔር ድርሻ እንደሚመስለን ምንም ጥያቄ የለውም፤ የእግዚአብሔር ድርሻ አለመሆኑን የምናውቀው እንድናደርገው በመታዘዛችን ብቻ ሣይሆን ልናደርገው በመቻላችን ነው። የእርሱ ድርሻ ቢሆን ኖሮ እኛ ልናደርገው ባልቻልንም ነበር። እኛ የእግዚአብሔርን ድርሻ አልፈን ልንሰራ አንችልም፤ እግዚአብሔርም የእኛን ድርሻ አልፎ ሊሰራ አይፈልግምና። እግዚአብሔር ለፍጥረት ውድቀት ምክንያት የሆነውን ሰው እንጂ ዘመንን አይዋጅም። ሰውን ከዋጀ በኋላ ግን የተዋጀው ሰው ዘመኑንና በዙሪያው ያለውን ፍጥረት እንዲዋጅ ያዘዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚሁ በኤፌሶን መልዕክት ውስጥ ስለመዋጀታችን አስደናቂ እውነት ገልጦልናል። በ1፡6 *‹‹በውድ ልጁም እንደ ፀጋው ባለጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት።››* በማለት በክርስቶስ ደም ከኃጠአት ዕዳና ከሰይጣን ግዛት እንደተቤዠን ይነግረናል። በመቀጠልም በ1፡14 ላይ *‹‹. . . እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፤ ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል።››* በማለት መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን በማደሩ የሚሰራውን የቤዛነት ሥራ ያሳየናል። በመጨረሻም በ4፡30 ላይ *‹‹ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።››* በማለት በእግዚአብሔር መለኮታዊ አሰራር በፍጻሜ ቀን

---

[4] 2ተሰሎ.2፡7 (የክፍሉ ሃሳብ ግልፅ ያልሆነና በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት የተለያየ ትርጉም የሚሰጠው ቢሆንም እኔ ግን ከልካዩ የክርስቶስ ቤተ-ክርስቲያን እንደሆነች አስባለሁ።)
[5] ሮሜ8፡19-22

ስለሚከናወነው ቤዛነት ያመለክተናል። እነዚህን በአማኞች ውስጥ ከጅማሬ እስከ ፍጻሜ በተከታታይ የሚከናወኑትን ሦስት የቤዛነት (የመዋጀት) ሂደቶች በትኩረት ስንመለከት አስደናቂ የእግዚአብሔር አሠራርን እናያለን። የጊዜ ሰሌዳቸውን በተመለከተ አንደኛው የተከናወነ፣ ሁለተኛው እየተከናወነ ያለና፣ ሦስተኛው ገና ወደፊት የሚከናወን ናቸው። ይህም ብቻ ሣይሆን የመጀመሪያው የመንፈሳችን፣ የሚቀጥለው የነፍሳችን (ሐሳብ፣ ስሜት፣ ፈቃድ) የመጨረሻውም የሥጋችን ቤዛነት እንደሆነ ማየት እንችላለን። የመጀመሪያው በክርስቶስ የመስቀል ሞት፣ ሁለተኛው መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን በማደሩ፣ ሶስተኛው ጌታ ከሰማይ በክብር ሲገለጥ የሚከናወኑ ተከታታይ የቤዛነት ሥራዎች ናቸው። እንግዲህ እግዚአብሔር ከውስጥ ጀምሮ ወደ ውጭ በስርየት ጀምሮ በክብር በሚፈጽመው በዚህ ቤዛነት በልጁ የሰራውን አስደናቂ ሥራ እንመለከታለን። ታዲያ መደነቅ ብቻውን በቂ አይሆንም፤ እኛ እንደተዋጀን በክፉው እጅ የወደቀውን ዘመን ልንዋጅ ይገባናል። በተደጋጋሚ "ዋጁን" ሲል የቆየው ጳውሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ "ዋጁ" ያለን ስለተዋጀንና መዋጀት ስለምንችል ብቻ ነው። ያልተዋጀ አይዋጅምና።

## <u>የጌታን ፈቃድ ማወቅ</u>

*‹‹ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ።›› ኤፌ*.5፡17

ዘመናችንን ስንመለከት ከምንጊዜውም ይልቅ ኑሮ የናረበት፤ በተቃራኒውም የሰዎች ፍላጎትና ምኞት የመጠቀበት ዘመን ነው። ስለዚህ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ሰዎች ኑሮአቸውን ለማሸነፍና፤ ምኞታቸውን ለማርካት ከሥራ ሥራ ይሯሯጣሉ፤ ከያዙት ይልቅ የተሻለ ሥራ ለማግኘት ማስረጃ ፍለጋ ከአንዱ የትምህርት ደረጃ ወደ ሌላው ለመሻገር ይደክማሉ። በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ የሚሳተፉ ኀሊናቸውን ለማርካት በየአገልግሎት ዘርፉ፤ በየኮሚቴው ገብተው ይወጠራሉ። መማር፤ መሥራት፤ ማገልገል እንከን የማይወጣላቸው መልካም ነገሮች ናቸው። ነገር ግን ሰዎች ስላደረጉት ብቻ በስሜት ተገፋፍተን የምናደርገው ከሆነ ችግር አለው። ለምንወስዳቸው ለእያንዳንዱ እርምጃዎች የጌታን ፈቃድ ካላስተዋልን ሞኞች እንሆናለን። ከእርሱ ጋር አልሰበሰብንምና ያከማቸን እየመሰለን እንበትናለን፤ በፍፃሜውም ያተረፍን መስሎን እንከስራለን። ታዲያ ምን እናድርግ? ዘመንን መዋጀት ማለት ያገኙትን ሁሉ በመስራት ያለዕረፍት መወጠር ሳይሆን ምን፣ መቼ፣ የት፣ እንዴት ማድረግ እንዳለብን የጌታን ፈቃድ በማወቅ መስራት ነው። የጌታን ፈቃድ ማወቅ ከሚቃጠል ሩጫ ተርፈን የሚያሸልም ሩጫ እንድንሮጥ ይረዳናል። የጌታን ፈቃድ በሁለት ክፍለን ልንመለከተው እንችላለን። አንደኛው የተገለጠ ፈቃድ ሲሆን ሁለተኛው የተሰወረ ፈቃድ ወይም አንደኛው በቃሉ ውስጥ በግልጽ የሰፈረና ለሁሉ የሚሰራ ሲሆን ሁለተኛው በግላችን የምንረዳው በፀሎትና የጌታን ፊት በመፈለግ የሚታወቅ ፈቃድ ነው። የመጀመሪያው እንዲገለጥልን ልንደክም አይገባም፤ ለተገለጠ ነገር መገለጥ መፈለግ መገልበጥ ያመጣልና። የእግዚአብሔርን ቃል በእግዚአብሔር መንፈስ በመማር አንድ ጊዜ የምናውቀው ሁልጊዜ የምንኖርበት፤ ሥፍራ፣ ባህልና የኑሮ ደረጃ የማይለውጡት ፈቃድ ነው። ሁለተኛው ግን እያንዳንዱ አማኝ በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ታግዞ በውስጡ በተቀመጠው ታቦት ላይ ኪሩቤል መላዕክት ለአፍታ እንኳን ዐይናቸውን ሳይነቅሉ ወደሚመለከቱት የሥርየት መክደኛ በመመልከት የጌታን ድምፅ ሲሰማና

ፈቃዱን ሲገነዘብ የሚረዳው ነው፡፡[6] ይህንን ዓይነቱን የጌታን ፈቃድ ለመረዳት የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታዎች የማይናቅ አስተዋፅኦ ቢኖራቸውም በዋነኝነት ግን በታደሰ አዕምሮ ሊታወቅ የሚችል ነው፡፡[7] እነዚህን ሁለት የፈቃድ አይነቶች በሚገባ ለመረዳት ምሳሌ ላክል፡፡ ከተማ ውስጥ መኪናችንን ለማቆም ብንፈልግ አንድ ነገር ማወቅ ይኖርብናል፤ ማቆም የተከለከለበትን ስፍራና ለመኪና ማቆሚያ የተመደበ ሥፍራን (parking Lot)፡፡ የተከለከለው መከልከሉ ግልጽ ነው፤ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ የባለሥልጣኑን ፈቃድ አውቀናል፤ ፈቃዱን ብንተላለፍም ቅጣት ይከተለናል፡፡ ነገር ግን ለማቆሚያ የተመደበው ሥፍራ ከገባን በኋላ የትኛው ጥግ ላቁም? ስንተኛ ፎቅ ላቁም? ጥላ ላይ ወይስ ፀሐይ ላይ ላቁም? ብንል፤ ያ የባለስልጣኑ ጉዳይ አይደለም፡፡የተፈቀደ ነውና፡፡ ነገር ግን ለእኛ የሚሻለንን ከጠየቅን ምክር ልናገኝ እንችላለን፡፡ ሌላ ምሳሌ ልጠቀም ዕድሜያችን ለማግባት ሲደርስ "ላግባ ወይ?" ብለን የጌታን ፈቃድ መጠየቅ አያስፈልገንም ይህ የተገለጠ የጌታ ፈቃድ ነውና፡፡ ደግሞም የማያምን/የማታምን ላግባ? ወይም ከጋብቻ በፊት ከጓደኛዬ ጋር ግንኙነት ልፈፅም? ብለን አንጠይቅም፡፡ ክልክል ነውና፤ ብንተላለፈውም የሚከተለን ቅጣት ይኖራል፡፡ ነገር ግን ማግባት እንዳለብን በተገለጠው የጌታ ፈቃድ ውስጥ ሆነን ማንን ላግባ? ብለን ልንጠይቅ እንችላለን፡፡ በጌታ እስከ ሆነ/ሆነች፣ ድረስ ማንንም ማግባት፣ አንዳች ችግር የለውም፡፡ ነገር ግን የጌታን ምክርና ጥበብ መጠየቅ እንችላለን፡፡ እነዚህ የሞትና የሕይወት ጉዳይ ሳይሆኑ የማትረፍና የመክሰር ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ሐዋርያው እያለ ያለው የትኛውን ፈቃድ እንደሆነ በድፍረት መናገር ባይቻልም፤ ይህኛውም ሆነ ያኛው ዋናው ቁም ነገር ፈቃዱን በማወቅ መሥራት ዘመንን ከመዋጀት አንፃር ያለውን ጠቀሜታ ያስገነዘበናል፡፡ ሐዋርያው ዘመንን ከመዋጀት አንጻር የጌታን ፈቃድ ለማሳወቅ ወደ ዝርዝር ጉዳይ አይገባም፤ ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ለሁላችን የሆነውን አንድ የጌታን ፈቃድ ሊያሳየን ይሞክራል፡፡ ይህንንም ለማሳየት የተጠቀመው በእርሱ ዘመን በኤፌሶን የነበሩ አሕዛብ ይለማመዱት ከነበረው የጣዖት አምልኮ ጋር በማነፃፀርና በማስተያየት ነው፡፡

## <u>መንፈስ ይሙላባችሁ</u>

> *‹‹መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤ ሁል ጊዜ ስለሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ፡፡›› ኤፌ.5፡18-20*

ከክርስቶስ ልደት ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት በሮም የተወለደው "ዳዮኒሰስ" የተሰኘው የጣዖት አምልኮ በኤፌሶንም ተንሰራፍቶ እንደነበር ይታመናል፡፡ ይህ ጣዖት "የወይን ጠጅ አምላክ" በመባል የሚታወቅ ሲሆን አምልኮው የሚቀርብለት ወይን ጠጅ በመጠጣትና በመስከር፤ ከዚያም በስካር ታጅቦ በመዝፈን (መጨፈር) እና ቅጥ ያጣ ርኩሰትን በመፈፀም ነበር፡፡[8] በዚህ የአምልኮ ሥርዓት ላይ ወይን ጠጅ የሚጠጣበት ዋና ምክንያት የወይን አምላክ (ዲዮኒሰስ) መገለጥን ወይም አብርሆትን ይሰጠናል ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡

---

[6] ዘፀ.25፡22
[7] ሮሜ 12፡2
[8] Keener, Craig S. The ivp bible background commentary, New Testament, p.550

የዚህ ጣዖት ማህበርተኞች ሴት ወንድ ሳይሉ በአንድነት ተሰብስበው እያወጉ፣ እየዘፈኑ፣ አንዳቸው ለሌላቸው ወይን ጠጅ እየቀዱና እየተገባበዙ ይጠጣሉ። በፍጻሜውም በውስጣቸው የሞላው ጠጅ ይቆጣጠራቸውና ራሳቸውን ይስታሉ፤ ከዚያም በእርኩሰት ይባልጋሉ፤ ፍጻሜውም ከልክ ያለፈ ብክነት ነው። በዚህ የአምልኮ ሥርዓት ውስጥ ከሚከሰተው ብክነት የተነሳ ግብረ-ገብ ያልነበረው የሮም መንግስት እንኳ እግድ ጥሎበት እንደነበር የታሪክ መጻሕፍት ይናገራሉ።[9] ብክነቱም በብዙ አቅጣጫ ቢሆንም አንዱ የጊዜ ብክነት ነበር። ይህን ተግባር የግሪኩ ቃል "አሶቲያ" ብሎ ሲጠራው፤ የቀድሞው አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ "ማባከን" አዲሱ መደበኛ ትርጉም ደግሞ "ብክነት" ብለውታል። የተለያዩ የእንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች "ዲባውቸሪ" ወይም "ፕሮፍሊጌሲ" በማለት ሲጠሩት፤ የአማርኛ-እንግሊዘኛ መዝገበ ቃላቶች "መበላሸት"፣ "መባለግ"፣ "ራስን መሳት" እና "ከመጠን ያለፈ ብክነት ውስጥ መግባት" በማለት ተርጉመውታል።[10]

ሐዋርያው ይህንን ምሳሌ ለመጠቀም ለምን ፈለገ? ይህ ዓይነቱ ችግር በቤተክርስቲያኒቱ ስለ ነበር አይመስለኝም። ነገር ግን ተደራሲዎቹ በቅርበት የሚያውቁትን ምናልባትም አንደንዶቹ ወደ ጌታ ከመምጣታቸው በፊት ይለማመዱት የነበረውን ምሳሌ በመጠቀም እንዴት ዘመኑን እንደሚዋጁ በማነፃፀርና በማስተያየት ለማስተማር የፈለገ ይመስላል። እኛም ለአካሄድ እንዲመቸን ከንጽጽሩ እንጀምር። ይህን መሰሉን ተግባር የሚፈፅሙት ሰዎች ማሕበር እንዳላቸው፤ በአንድነትም ተሰብስበው ወይን ጠጅ እንደሚከፋፈሉ፤ ይህንንም በማድረግ እርስ በርሳቸውም ሆነ ከሚያመልኳቸው የአጋንንት መናፍስት ጋር ሕብረት እንደሚያደርጉ፤[11] እኛም ሕብረት አለን፤ በአንድነትም ተሰብስበን የክርስቶስን ሕይወት እንካፈላለን፤ በዚህም ከእግዚአብሔርም ጋር ሆነ እርስ በርሳችን ሕብረት እናደርጋለን[12]፤ ይህም ሕብረት የሚካሄደው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው።[13] እነርሱ በወይን ጠጅ የሚሰክሩት ዘወትር በተሰበሰቡ ቁጥር እንደሆነ ሁሉ፤ ለእኛም በመንፈስ መሞላት የከዕለታት አንድ ቀን ልምምድ ሳይሆን ቀጣይነት ያለው የዘወትር ጉዳይ መሆኑን ያመለክተናል። እነርሱ ጊዜ ወስደው ወይን ጠጅ በጠጡ ቁጥር በውስጣቸው የሞላው ጠጅ እንደሚቆጣጠራቸው ሁሉ፤ እኛም በውስጣችን የሚሞላው መንፈስ ቅዱስ ይቆጣጠረናል። በእነዚህ አሕዛብ ስብሰባ ወይን ጠጅ የሚጠጡት የተወሰኑ ምርጦች ሳይሆኑ የአምልኮው ተሳታፊዎች ሁሉ እንደሆኑና በእንዲህ አይነቱ ስብሰባ ወይን በመጠጣት አለመሳተፍ ባይተዋር እንደሚያደርግ ሁሉ፤ በእኛም ዘንድ ዘወትር በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የጥቂት ምርጦች ልምምድ ሳይሆን፤ የወንጌል ማሕበርተኞች ሁሉ ልምምድ እንደሆነ ያሳየናል። እንዲያውም "መንፈስ ይሙላባችሁ!" የሚለው ቃል ምክር ሳይሆን ትዕዛዝ መሆኑን የግሪኩ ግሥ በግልፅ ያስረዳል። እነርሱ ወይን ጠጅ ሲሞላባቸው እንደሚዘፍኑና እንደሚጨፍሩ፤ እኛም መንፈስ ሲሞላብን በመዝሙር፣ በዝማሬ፣ በማኅሌት፣ በቅኔ እርስ በርሳችን እንነጋገራለን፤ ለጌታም ከልባችን እንዘምራለን፤ እናመሰግናለን። እዚህ ጋ በጳውሎስ አጻጻፍ ውስጥ ልብ ማለት ያለብን አንድ ቁም ነገር አለ፤ ያም ስለዝማሬ የጻፈውን ሃሳብ ለሁለት መክፈሉ ነው። ***‹‹በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ›› ‹‹ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ››***

---

[9] Vos, Howard Fredric,1925 Wilson's New illustrated Bible manners & customs: how the people of the Bible really lived /Howard F. Vos. p. 610

[10] Leslau, Wolf English-Amharic context dictionary

[11] 1ቆሮ.10፡14-22

[12] 1ዮሐ.1፡1-3

[13] 2ቆሮ.13፡14

በማለት። የመጀመሪያው የጎንዮሽ ግንኙነትን የሚያሳይ፤ የእርስ በርስ ዝማሬ ሲሆን ሁለተኛው ወደ ላይ ያለንን ግንኙነት እርሱም ለጌታ የምንዘምረው ዝማሬ የሚያመለክት ነው። ልብ ሊባል የሚገባው የጎንዮሹ ዝማሬ ለወደላዩ ዝማሬ ወይም የእርስ በርሱ ዝማሬ ለጌታ ለምናቀርበው ዝማሬ መሠረት መሆኑ ነው። የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ቅዱሳን ለጌታ ብቻ ሣይሆን እርስ በርሳቸው የሚዘምሩት ዝማሬ ነበራቸው። በአሁኑ ዘመን ቤተ-ክርስቲያን ይህ ልምድ እምብዛም ስለሌለ ግር ቢለን አያስደንቅም። ጳውሎስ ይህን ለመግለፅ ሦስት የተለያዩ ቃሎችን ተጠቅሟል፤ መዝሙር፣ ዝማሬ፣ መንፈሳዊ ቅኔ። እኛ ስለ መዝሙር የምናውቀው በዜማና በግጥም ሌሎች የዘመሩዋቸውን መዝሙሮች እየመረጥን መዘመር ነው። ነገር ግን ስለ መዝሙር ከዚህ በዘለለ ልንረዳ ይገባል። የመጽሐፍ ቅዱሳችን ረጅም መጽሐፍ የሆነው “መዝሙረ ዳዊት” ከሌሎች መጽሐፍት የሚለይበት አንዱ ባሕሪ፤ ሌሎቹ በዋነኝነት እግዚአብሔር ለሰው የተናገረባቸው ሲሆኑ ይህኛው ግን ባመዛኙ ሰዎች ለሰዎች ስለ እግዚአብሔር የተናገሩበት መሆኑ ነው። መዝሙርና ዝማሬ መንፈሳዊ ቅኔ ሁል ጊዜ የግድ ዜማ አያስፈልገውም። የመዝሙረ ዳዊት ዝማሬዎች ከተወሰኑት በስተቀር ሁሉ ባለ ዜማ እንዳልሆኑ ማለት ነው። ስለዚህ ተሰብስበን በተከሸኑ፤ ባማሩ፣ በተዋቡና በመንፈስ በተቃኙ ቃላት እርስ በርሳችን ስንነጋገር ለጌታ በመንፈሳዊ ቅኔ እየተቀኘን እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል። በዚህ ሁኔታ ስለ ጌታ በልባችን የፈለቀውን መገለጥ እርስ በርሳችን ስንነጋገርና በልባችን በመንፈስ የተጠመቀውን ያማረ የወይን ጠጅ ስንገባበዝ መንፈስ እየሞላብን ይሄድና በፍፃሜው በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ሆነን ለጌታ እንዘምራለን፤ አብንም በኢየሱስ ስም ስለ ሁሉ እናመሰግናለን።

ከንጽጽሩ ወጥተን ወደ ማስተያየቱ ስንመጣ ከዳዮኒሰሳዊያን የምንለይባቸውን በርካታ ነጥቦች እናገኛለን። ከነዚያም መካከል ጥቂቱን ለመመልከት እንሞክር። እነርሱ ወይን በመጠጣት መገለጥ እንደሚያገኙ ያስባሉ፤ በመሰረቱ የወይን ጠጅ ያሰክራል፤ ያጃጅላል፤ ያፈዛል፤ የማሰብን አቅም ይከላል እንጂ አያነቃም፤ የማሰብንና የማወቅን እምቅ አቅም አይቀሰቅስም። እኛ ግን መንፈስ ቅዱስ ሲሞላብን መንፈሳችንም አዕምሮአችንም ይነቃል፤ በመለኮታዊ ዕውቀት እንሞላለን፤ ያም በመረዳት ወደ ሆነ ምሥጋናና አምልኮ ይመራናል። ሌላው እነርሱ በወይን ጠጅ ሰክረው ሲዘፍኑ ራሳቸውን ይስታሉ፤ ይንገዳገዳሉ፤ ይወድቃሉ፤ ይነሳሉ፤ የማይገባቸውንም ያደርጋሉ። እኛ ግን በውስጣችን የሚሞላው መንፈስ ከሁሉ አስቀድሞ ራስን የመግዛት መንፈስ ነውና ራሳችንን እንገዛለን እንጂ አንስትም።[14] ስለዚህ በመንፈስ ሆነን የምናደርገውን ሁሉ በሥርዓት ማድረግ ይጠበቅብናል ደግሞም እንችላለን።[15] ለዚህ ነው ሐዋርያው አንቀጹን ሲደመድም *‹‹ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ›› 5፡21* በማለት መንፈስ ሲሞላብን ለጌታ ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳችንም በክርስቶስ ፍርሃት እንደምንገዛ የሚነግረን። ሌላው እነርሱ በወይን ጠጅ ሰክረው እርስ በርሳቸው በፍትወት ሲቃጠሉና ሩካቤ ሥጋ ሲፈፅሙ፤ እኛ ግን በመንፈስ አንድነት የሕይወት ተራክቦ እንፈጽማለን። ይህንንም በመካከላችን የሚፈፅመው መንፈስ እንደስሙ “ቅዱስ” ነውና ሕብረታችን በቅድስና የተሞላ ነው። በመጨረሻም እነርሱ በመስከር ጊዜያቸውን ሲያባክኑ እኛ ግን በመንፈስ በመሞላት፤ እርስ በርሳችን በመተናነጽና ጌታን በማምለክ ዘመናችንን እንዋጃለን።

---

[14] ገላ.5፡22፤ 2ጢሞ.1፡7
[15] 1ቆሮ.14፡32፣40

በመጨረሻም ወደ ማጠቃለያ ስንመጣ በኤፌሶን 5:15-21 ባሉት ቁጥሮች የሰፈረው የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት የሚያስገነዝበን ዋና ቁምነገር የጌታን ፈቃድ አስተውለን፤ በጥበብ እየተመላለስን ዘመናችንን ለመዋጀት የጌታን በጎነት የምንካፈልበትና የምናካፍልበት የቅዱሳን ሕብረት ወሳኝ መሆኑ ነው። ዘመኑ ረቆ በግራ በቀኝ ውጥረት ቢበዛና ለብዙ ነገር ጊዜ ብናጣ እንኳ ጊዜ ልናጣለት የማይገባ ዘመን የመዋጃ ሥልት በቅዱሳን ሕብረት ከጌታና ከሕዝቡ ጋር የሁለትዮሽ ግንኙነት የማድረግ ጉዳይ ነው። በቀን ወስጥ ብዙ ክፋት፤ ስፍር ቁጥር የሌለው ርኩሰት አፀያፊ ጢሱ ወደ ሰማይ በሚትጎለጎልበት ዘመን፤ የጌታን ቸርነት ከቀመሱ ቅዱሳን አንደበት ከሚፈልቅ ዝማሬ፤ ውዳሴ፤ ማኅሌትና፤ መንፈሳዊ ቅኔ በስተቀር ክፉ ሽታውን የሚለውጥ ምን መልካም መዓዛ አለ?! ከክፋት ሽታ ቀድሞ የምስጋናችን መዓዛ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ይደርስ ዘንድ በአንድነት በመሰብሰብ እርስ በርሳችን ቸርነቱን እንነጋገር፤ ለጌታም ከልባችን እንዘምር። ዘመን መዋጀት ይሏችኋል ይህ ነው። መልካም አዲስ ዘመን!!!

ያሬድ ጥላሁን
(ለፈረንጆች 2009 ዋዜማ)
አዲስ አበባ